# <u>የ እንትጮ ፕሮፌሰር፤ሲፈናጠር - እንደፌንጣ!</u>

ከዳግማዊ አደፍርስ

የዚህ ፅሑፌ ምክንያት ባለፈው ሳምንት መገባደጃ ላይ አንድ የሬዲዮና ቴሌቪሺን ጣቢያ እንደልማዱ መስፍን ወልደማሪያምን መፅሐፍ ፃፈ በሚል ምክንያት ለቃለ ምልልስ አቀረብነው ብለው ያንኑ መያዣ መጨበጫ የሌለው የስድብ ናዳ ከአንዱ ጫፍ ወደ ሌላው እየተስፈነጠረ እንዲያዥጎደጉድ ማድረጋቸው ነው።

ያ ለውድ ሀገርና ለውድ ወገኖቹ መልካም ምኞትን ሰንቆ ታግሎ ስንት አይከፍሉ መስዋዕትነትን የከፈለ ትውልድና አርበኛ ዜጋን ሲሰድብ የነበር ሰው አቅርበው አሁን ደግሞ መላውን ህዝብ አስሞለጩት። ይህ ለከት የሌለው ፕሮፌሰር ነኝ ባይ የኢትዮጲያ የመሬት ስሪት እስከዛሬም ድረስ ያልተስተካከለ አርሶ አደሩን ለዘመናት በመሬት አልባ ገባርነትና ጭሰኝነት አበሳውን እንዳላበላውና በአምራችነቱ ላይ ከፍተኛ ጫና እንዳልነበረው ሁሉ "ከወሎ እስከኢሉባቡር ጥናት አድርጌ ገበሬው በርከት አድርጎ የማያመርተው ከፍ አድርጎ ለባለመሬቱ ላለመክፈል መሆኑን ደርሼበታለሁ" ያለና መላውን የኢትዮጵያ አርሶ አደር በልግመኝነት ለመወንጀል ትንሽም ይሉኝታ ያላደረበት ነው።

ብዙ ብዙ የሚላቸውን አስተዛዛቢ ነገሮችን ማንሳት ይቻላል። በአንድ ወገኔ ሰሜን ሸዋ በሌላው ወልዲያ ነኝ ሲል በደንብ ተደምጦ ሳያበቃ በቅፅበት ተስፈንጥሮ" እኛ ከአድዋ እንትጮ ነን" ያለስ አይደል? ሆኖም ግን በዚህ ፅሑፌ ላይ ማንሳት የፈለግሁት ይህን ይህን አይደለም። ዋናው ልሄድበት የፈለግሁት በዚህ የሰሞኑ ጥያቄን መልስ ላይ የ1966 ዓ.ም የመርማሪ ኮሚሽንን በሚመለከት ያደርገው መቀላመድ ላይ ነው።

ከሁሉም ከሁሉም በጣም ያስደነቀኝ ዶክቶር ፕሮፈሰሩ እንትጮዓዊ ዓይኑን በጨው አጥቦ ደርግ የመርማሪ ኮሚሽኑን በማቋቋሙና ስራውን በመቆጣጠሩ ላይ ምንም ሚና የአልነበረው ለማስመሰልና ያንን ኮሚሽን የአፄው መንግሥት የሾመው አድርጎና ሞስሶ ለማለፍ መሞከሩ ነው። ለነገሩማ ይህንን ሰው መድረክ ሰጥተው የሚያቀባዥሩት "ጋዜጠኞች" በወቅቱ ያልነበሩ ከመሆናቸው በላይ ለእንደዚያ ያለ ጥያቄና መልስ በቂ ምርምርና ዝግጅት የማያደርጉ መሆናቸውን በሚያሳይ ደረጃ የሚዘጋጁ በመሆናቸው ምክንያት እነርሱን ሞሳ ብሎና ሸውዶ ማለፍ ስለሚችልበትና ሁሉም በወቅቱ ያልነበረ፤ የነበረው ሁሉ ደግሞ ያለቀ ወይም የአሁኑ ትውልድ ደግሞ ለጥናትና ምርምር ፍላጎቱ የሌለውና የጋቱትን ሁሉ የሚጋት ነው ተብሎ የተባለ በሚያስመስል ድፍረት መሽምጠጥ የተቆራኘው ሆነ።

እነዚሁ "ጋዜጠኞች" ትጉህና ለሙያው ክብር ያላቸው ቢሆኑ ኖሮ ለእንዲህ ዓይነቱ ጥያቄና መልስ በተለይም ከእንዲህ ዓይነት ዋሾና አወዛጋቢ ሰው ጋር ለማድረግ ሲወጥኑ በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ በተገባቸው ነበር። ያንን ለማድረግ ደግሞ ብዙም ሳይጓዙ እዚያው ካፒቶል ሂል ላይብራሪ ኦፍ ኮንግረሥ ብቅ ቢሉ ከበቂ የፅሁፍ መረጃዎች በተጨማሪ የነመስፍን ወልደማሪያም የምርመራ ኮሚሲዮን ምርመራውን ያካሔድበት የነበረበትን ዘግናኝና አሰቃቂ የሆነውን ድምፅ ቅጂ ከድምፅ ማህደር ያገኙ ነበር። ታዲያ ምን ያደርጋል? ይታደሉታል እንጂ አይሸምቱት!

ለነገሩማ አሁን ሳየው ሳየው አብዛኛዎቹ እርሱ ያስተማረንና የመለመለን ብለው የሚመፃደቁ አይደል? በቅርቡ "ያ ትውልድ የኔን ትውልድ ፍርሀትን አጋበበት" ብሎ ያለ የቅጥር ጋዜጠኛ ፅሑፍ አገኘን ብለው ድምፃቸው ጣሪያ እስኪነካ ከፍ አድርገው አንብበው ልቤን በሳቅ ሲያፈዱትስ አልነበር?

ለማንኛውም "ሲያደባ ያንቀላፋ ቢቀሰቅሱት አይሰማም" ተብሏልና ለጋዜጠኞቹ እንኳን ባይሆን ለአንባቢዎችና አድማጮች ማመሳከሪያ ይሆን ዘንድ በወቅቱ አዲስ አበባ የነበረ የአሜሪካን ኤምባሲ ባልደረባ ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፅ/ቤትና ለተለያዩ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ውስጥ ለሚገኙ ኤምባሲዎች የላከውንና በዊኪሊክ ሰነድ ይፋ የሆነውን የኬብል መልዕክት መረጃ ድረ-ገፅ ላስቀምጥ https://wikileaks.org/plusd/cables/1974ADDIS08028_b.html. ይህን ነው እንግዲህ መስፍን ችክ ድርቅ ብሎ የሾመኝ የአፄው መንግሥት ነበር የሚለው። ሐምሌ 1966 ላይ ያፄው መንግሥት ያለ ይመስል! ፓርላማው ነው? ፖሊስ ሰራዊት ነው? ክብርዘበኛ ነው? ማን ያልወከለና ያልሰየመ ነበር? ማን እንደወከላቸው ሳታወቅ እነሁሴን እስማኤል፤ አቶ ለማ ጉተማና ሌሎችም ገብተውበታል።

ይህንን ኮሚሺን በማቋቋም የ ፓርላማው ሥልጣን የጎላ በነበርና ደርግ ምንም እጁን ያልዘፈቀበት ቢሆን ኖሮ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም በወታደሮቹ አዋጅ የአፄው ንግስና ሲደመሰስና ለዕረፍት እንደወጣ ሳይመለስ በዚያው አዋጅ የፈርሰው ፓርላማ ሲበተን የኮሚሺኑ ህልውና በምንም ዓይነት ህጋዊ መስፈርት መቀጠል አልነበረበትም። የኮሚሽኑ መሰንበት ተፈጣሪነቱም ሆነ ተጠሪነቱ በማን ለማን እንደሆነ ለጋዘጠኞቹና ለፕሮፌሰሩ ባይታያቸው የሆነ ችግር አለ ማለት ነው።

ወደሚቀጥለው ነጥቤ ከመሸጋገሬ በፊት በነካ እጅ ይህን ሌላ ድረ-ገፅ https://wikileaks.org/plusd/cables/1974STATE159026_b.html ጆባ ብዬአችሁ ልለፍ - መስፍን ማለት ማን እንደሆነ እንድታዩልኝም ነው።

ልቀጥል- አሁን ደግሞ የትርጉም ሥራ ውስጥ ልግባና በአንድ ሌላ ድረ-ገፅ ላይ ያገኘሁትንና በወ ቅቱ የነበረውን ሁኔታ ቁልጭ ባለ መልክ ያሳያልና ተርጉሜ ላቅርብ። በትርጉም ሥራው መልዕክቱን ካዛባሁኝ ሙሉ ኃላፊነቱን ወስጄ እግረመንገዴንም የፅሑፉን አቅራቢዎች ተገቢውን ይቅርታ ጠይቄ ራሴን ለማረም እጥራለሁ እንጂ በፍፁም አልታበይም። "ዕውቀት አንፃራዊ ነው" ያለው ማን ነበር?

ለማንኛውም ድረ-ገፁ www.africaspeaks.com/reasoning/index.php?topic=5171.0 ሲሆን ትርጉሙ እንዲህ ይቀጥላል።

## “ የአፄውን የቀድሞ ባለሥልጣናት ለመመርመር የተፈጠረው የ1966 መርማሪ ኮሚሽን

ተፃፈ 30 ግንቦት 2008፤ 07፡28፡ 21

1966 ለኢትዮጵያ የ አዲስ ዘመን ምዕራፍ መከፈቻ ዓመት ነበር። የአፄው መንግሥት ደርግ ተብሎ በዝቅተኛ ወታደራዊ መኮንኖች የተዋቀረና ኋላ ኋላ ላይ ጥቁሩ ስታሊን ተብሎ ይጠራ በነበረው በኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማሪያም በተመራ ስብስብ ተተካ። ቀጥሎም ደርጉና የግድያ ስኳዶቹ በሀገሪቱ በፍፁምታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በደም የጨቀየ ዘመንን አስቆጠሩ።ሥልጣንቸውንም በቀድሞው የአፄው ባለሥልጣናት ላይ በማተኮር ሀ ብለው ጀመሩት። ደርጉ በአንድ ወገን ባለሥልጣናቱ ፈፅሙ የሚባልን አስተዳደራዊ ጥፋት የሚጣያራ ኮሚሺን እንዲቋቋም እያደረገ በሌላ በኩል እዚያው በዚያው ወንጀለኞች አድርጎአቸው በባለሥልጣናቱ ላይ አሉታዊ ፕሮፓጋንዳውን ያስነካው ገባ።

በዚህ ጊዜ የመስፍን ወ/ማሪያምና የበረከት ሀ/ስላሴ በቀላሉ ተሸሎክልከው በኮሚቴው ውስጥ መግባትና ሊቀመናብርት መሆን ብዙዎችን ያስገረመ ክስተት ነበር። በረከት ሀ/ስላሴ ከአፄው የቀድሞ ባለሥልጣናት አንዱ የነበረ ሲሆን የአሁኑ ፕሮፌሰር የያኔ አቶ፤ መስፍን ወ/ማሪያም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የጂኦግራፊ አስተማሪ ነበር።

ምንም የአሰያየማቸው ሁኔታ እስከዛሬም ድረስ ግልፅነት የጎደለው ቢሆንም የታሣሪዎቹን ቤተሰብ አባላት ጨምሮ ብዙዎች የምርመራ ሥር ዓቱ አካሔድና የሊቀመናብርቱ አያያዝ ሚዛናዊና ተገቢውን ክብር በተላበሰ ሁኔታ ይከናወናል የሚል እምነት አሳድረው ነበር። ሆኖም ግን ምን ያደርጋል ከሆነው ነገር በከፋ ሁኔታ ከሃቅ የተጣላ ሁኔታን መከሰትማሰብ አይደለም ማለምም እንኳን ቢሆን ያስቸግራል። ያኔ የታየውን ሁኔታ መግለፅ የሚቻለው"ሊቀመናብርቱ በቅናት፤ በቂም-በቀልና ደርጉን በማስደሰት ላይ ባተኮረ ስንኩል ህሊና የታጨቀ ግላዊ አጀንዳ ነበራቸው" በማለት ነው ።

ሊቀመናብርቱ አንዳችም ይሉኝታ ይባል ነገር አልነበራቸውም በሚያስብል ደረጃ የታሳሪዎቹና የቤተሰቦቻቸው የተባለ ነገር - ወንበሮች፤ ጠረጴዛዎችና ልብሶቻቸው ሳይቀሩ ነበር እንዲያስመጡ ሲያዟቸው የነበሩት። ከፀሀፊ ታዕዛዝ አክሊሉ ሀ/ወልድ ጀምሮ ሁሉም ታሳሪዎች - ለማዋረድ በታቀደ ሁኔታ - አንገት ደፍተው በሊቀመናብርቱ ፊት እንዲመላለሱ ተገደዱ። የምርመራ ስልታቸው የአጠያየቅ ዘዴያቸውና የድምፅ ግነት የታሳሪዎቹን ዕድሜና አገልግሎትዘመን በጭራሽ ምንም ታክል ግምት ውስጥ ባልጨመረ መልኩ ሆን ተብሎ ለማዋረድ የታቀደ ዓይነት ነበር። የዚያ ሁሉ ዓላማም የባለሥልጣናቱን በጎ ሥራዎች ሁሉ ለማጣጣልና የአፄውን ዘመን ክንዋኔዎች ለማራከስ ነበር። ሊቀመንብርቱ በአንዲት ምሽት ቅፅበት ይደርጉ ተናካሽ ውሾች ሆነውት አረፉ። እንዲያ ያለ ባህሪና ድርጊት ከነመንግሥቱ ዓይንቱ የሚጠበቅ ነገር እንጂ በረከት ሀ/ሥላሴንና መስፍን ወ/ማሪያምን ከመሰሉ እያንዳንዲ የሚሏትና የሚያደርጓት ሁሉ የቀድሞ ባለሥልጣናቱንና የቤተሰቦቻቸውን መፃኢ ዕጣ ፈንታ ለመወሰን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይረዳሉ ተብለው ተጠብቀው ከነበር ሰዎች የሚጠበቅ አልነበርም።

ከዚያም በላይ አንደኛው የምርመራ ዘርፍ ነው ተብሎ ታሣሪዎቹ - ቤሰሰቦቻቸው ሳይቀሩ -ያለ የሌለ ንብረታቸውን የሚዘረዝሩበት ቅፅ ተዘጋጅቶ እንዲሞሉ ተገደዱ። ነገር ነገሩማ የቀድሞ ባለሥልጣናቱን 'ሌባ' ብሎ በህዝብ ዘንድ ለማሳጣት በደርግና በሊቀመናብርቱ ታቅዶ የተከናወነ የህዝብ ግንኙነት መተጣጠፍ መሆኑ ነው። በርግጥም ደርግና ኮሚሺኑ በነዚህ ቅፆች አሞላልና በምርመራው ክንዋኔ ወቅት ሲካሔዱ በነበሩት የአጠያየቅ ዘይቤና ምላሾች የትጋጋለ ሞቅ ሞቅ የመፍጠር ጥበቡ ተሳክቶላቸው ነበር። በዚሁ ድርጊትም ዶክተር በርከትና አቶ መስፍን፤ እንደነ አክሊሉ ሀ/ወልድ ያሉ አቅማቸው ከሚችለው በላይ ሲሰሩ የነበሩ ባለሥልጣናቱን የማዋረዱ ሥራ እንዳቀዱት ተከናወነላቸው።

በዚህ አኳኋን ቀጥሎ ህዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ባለሥልጣናቱ ታጉረው ከነበሩባቸው የዕስር ክፍሎች ስማቸው በወታደሮች እየተጠራ የወጡ 60 ሰዎች የዚያኑ ምሽት ተረሸኑ። “ የመንግሥቱ ትዝታዎች” በሚል ርዕስ የተፃፈ መፅሐፍ ውስጥ፤ የቀድሞው ፕሬዚደንት መንግሥቱ ኃ/ማሪያም በሰጠው የጥያቄዎች መልስ ላይ “ምርመራው እንዴት እየተካሔደ ነው” ብለን ብንጠይቃቸው "እናንተ የያዛችሁት ጠመንጃኮ እኛ ከያዝነው ብዕር ይበልጣል" ብለው ሊቀመናብርቱ የፍጅቱን መደላድል መሰረት ጣሉልን (በአሜሪካን ግቢ ቋንቋ ሲነገር ደግሞ - ወሰውሰውናል -) ይላል። መንግሥቱ አለ የተባለው ነገር ግምት ተሰጠውም አልተሰጠው የነዚያ ሊቀመናብርት አድራጎት በነዚያ በተረሸኑትም ሆነ ከዚያ በኋላ ለረጅም ዓመታት በዕሥር በማቀቁት ባለሥልጣናት ዕጣ-ፈንታ በመወሰኑ ጉዳይ ላይ የጎላውን ድርሻ እንዳበረከተ ሊካድ የሚችል አይደለም።

መቼም አንዳንዴ የሰው - በተለይም የያኔውን ዓይነት ድርጊት-ከፉ ኮሚሺንን የመራ ዓይነት ሰው - መገለባበጥ አስገራሚ ነው። መስፍን ወ/ማሪያም እነዚያን ተከላካይ አልባ የቀድሞ ባለሥልጣናትን ሲያሰቃይ እንዳልነበረ ሁሉ የኢትዮጵያ ሰባዊ መብት ጉባኤን (ኢሰመጉ) አቋቁሞ የሰባዊ መብት ተከላካይ ሆነና ኢሰመጉን በአስገራሚ ሁኔታ መራው።

ያ ሁሉ አልፎ ደግሞ የደርግ ዘመን አብቅቶ የደርጉ ባለሥልጣናት የክስ ሂደት ይካሄድ በነበረበት ወቅት መላውን አገር አጃኢብ ባሰኘ ሁኔታ በተከሳሾቹ አንፃር ይካሄድ የነበረው የፍርድ ሂደት ተቋርጦ በነፃ ይለቀቁ ዘንድ ጠየቀ። ይህ አንዳንዶች የፖለቲካ ሸክም ብለው የሚፀየፉት መስፍን ወ/ማሪያም አሁን ደግሞ ቀስተ ደመና በሚል ስም ገኘውን ፓርቲ እቃወማለሁ ያለ የፖለቲካ ፓርቲ ከፍተኛ አመራር አባል ሆኖአል። ያንን - ሆን ተብሎ - የአፄውን መንግሥት ባለሥልጣናት ለማዋረድ ተቋቁሞ የነበረን ኮሚሺን የመራው መስፍን ወ/ማሪያም አሁን ተገልብጦ የአፄውን መንግሥት ሲያሞጋግስ ይታያል። "የአፄው መንግሥት ከፍተኛ ግምት ያላቸው ነገሮችን አከናውኖአል። ተከትለው የመጡት መንግሥታት ሥራዎች እንኳ አይስተካከሉትም።" ሲል እየተደመጠ ነው።

ልብ በሉ! ያኔ እነፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀ/ወልድን ሲያበሻቅጥ በነበረ ጊዜ ቅንጣት ታክል እንኳ ይህ ሀቅ አይታየውም ነበር። ዛሬ ዛሬ የአፄው መንግሥት በህዝብ ዘንድ በበጎ መወሳት ሲጀምር ይህ ሀፍረት-ቢስ አድርባይ በአዲሱ ባቡር ላይ ሊሳፈር ቢንጠላጠል ማንም መገረም የለበትም።

ምን ያህል ሊደባብቁት ቢከጅሉ ታሪክ ሁሌም ራሱን ገልፆ የሚያሳይበት አስገራሚ ወቅቶች አሉት። እና ምንም አክሊሉ ሀ/ወልድና የሥራ ተጓዳኞቹ ካለፉ አመታት ቢቆጠሩም ያደረጉት ሆነ የተደረገባቸው - በተለይም በዚያ ከፉ የሆነ መርማሪ ኮሚሺን የደረሰባቸው ሰቆቃ- ለሁሌም ሳይረሳ ይኖራል። ” የትርጉሙ መጨረሻ!

ሀቁ ይህ ነው - እንደምንጭ ውኃ ጥርት ያለው ሀቅ። ሌላው በሺህ መፅሐፍ ቢጠርዙት ምንም ሚዛን የማያነሳ ገለባ ነው። ገለባ ደግሞ የህዝብን ትግል የማደናቀፍ ተልዕኮው እዚህ ግባ የሚባልም አይደለም።

ዳግማዊ አደፍርስ